# ዜና መጽሄት Newsletter

መስከረም 2007

September 2014

Emmanuel Development Association (EDA)
Tel: +251-116-476181 Mob: +251-911-226260
Fax: +251-116-460199 Web: www.edaethiopia.org
P.O.Box 908 Addis Ababa, Ethiopia

AMREF in Ethiopia
Tel. +251 1-16-63 0541
P.O.Box 20855



Musical show



በመጀመሪያው እትማችን ስለ ሰሜን ሸዋ ወጣቶችና ምቹ የሆነ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት፣ እንዲሁም በሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙት ሦስት ወረዳዎችና አንድ የከተማ አስተዳደር ማለትም በሞረትና ጅሩ፣ በቀወት፣ በሲያደብርና ዋዩ ወረዳዎችና በሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር በስነተዋልዶ ጤና ዙሪያ እየተገበርን ስላለው ፕሮጀክት ዝርዝር አላማዎች፣ ስለተከናወኑ ዋና ዋና ተግባሮችና ስለ ስነተዋልዶ ጤና ምንነት ማብራራታችን ይታወሳል፡፡

In our first release, it is to be recalled that we discussed about Youth and Youth Friendly Reproductive Health (RH) Service and about the essence of the program and activities accomplished, objectives of our ongoing project being implemented in MoretinaJiru, SiadebirinaWayu, Kewot Woredas and ShoaRobit Town Administration of North Shoa Zone in Amhara Region.



Question & Answer in school



Peer educators and Focal persons training

ካለፈው በመቀጠልም እነሆ የሦስተኛውን ሩብ ዓመት የፕሮጀክት ትግበራ ዜና የያዘና ከጽንስ ማስወረድ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ጥንታዊ የፍልስፍና ሰዎች ስለ ውርጃ ያራምዱአቸው የነበሩትን ጽንሰ ሃሳቦች እንዲሁም በዘመኑም ያሉ የተለያዩ ሀገራት መንግስታትና የኢትዮጵያ መንግስት ጽንስ ማስወረድን አስመልክቶ ያስቀመጧቸውን ድንጋጌዎች የሚያብራራ መጽሄት ይዘን ቀርበናል፡፡

In continuation of our quarterly newsletter, we are once again coming to you with some of our quarterly project implementation news and antiquity philosophers' perception about abortion, and thereby laws of the contemporary world nations and Ethiopia on abortion and related issues.



Young women BDS & vocational skill training



Question & Answer in school

## የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

### የአቅም ግንባታ ሥራዎች፡

በዚህ ሩብ አመት ማለትም ከሃምሌ እስከ መስከረም ወር ባለው ጊዜ ውስጥ 4 የስነ ተዋልዶ ጤና ክበቦችን በስልጠናና በሚኒሚዲያ ቁሳቁሶች በማገዝ ለማጠናከር ጥረት ተደርጔል፡፡ 527 ለሚሆኑ አቻ ለአቻ ትምህርት ሰጪዎች፤ ለአስተማሪዎች፤ ለጤና ሠራተኞች፤ ለወጣት ማህበር አመራሮች፤ ለጤና ልማት ሠራዊት አባላት፤ ለጤና አገልግሎት ሰጪዎች፤ ሥራ አጥ ለሆኑ ወጣቶች፤ለወጣት ማህበራት አባላት እና የክበባት መሪዎች በስነተዋልዶ ጤና፤ በእናቶችና ህጻናት ጤና እና በፀረ ኤች አይቪ ኤይድስ አገልግሎት ዙሪያ፤ በስነ-ጾታና ለወጣቶች ምቹ በሆነ ስነተዋልዶ ጤና ላይ ያተኮረ አገልግሎት አሰጣጥና አገልግሎቱን በፕሮግራም መቅረጽ ጨምሮ፤ በምርምር፤ በክትትልና ግምገማ እንዲሁም በወጣት መር ተጠያቂነት ሥርዓት ዙሪያ ከ 5 እስከ 10 ለሚሆኑ ቀናት ሰፋ ያለ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

## Major Activities accomplished

### Capacity Building

In this quarter, July through September 2014, we have supported 4 RH clubs providing them with various capacity enhancement trainings and mini-media equipments. 527 peer educators, teachers, health workers, youth leaders, Health Development Army (HDA) members, health service providers, unemployed youth, youth associations' members and club leaders out of whom 215 were female received a 5 to 10 days training on Sexual Reproductive Health (SRH), integration of Maternal Neonatal Child Health (MNCH) and Anti-HIV/AIDS services, gender sensitive and Youth Friendly Service (YFS) provision, SRH service programming, research, Monitoring & Evaluation (M&E) and, youth-led accountability systems.

### የግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች፡



Musical show

በተጨማሪም በቀወት፤ በእነዋሪ በደነባና በሸዋሮቢት ከተሞች በትምህርት አዘል ሙዚቃዊ ድራማ በመታገዝ 5,300 (3,500 ወንድ 1,800 ሴት) ለሚሆኑ ወጣቶች በስነተዋልዶ ጤናና በኤች አይቪ ዙሪያ ለ ለ10 ቀናት የግንዛቤ ፈጠራ ሥራ ተካሂዷል፡፡ ከ5300 ወጣቶች ውስጥ ዘጠና በመቶ የሚሆኑት እድሜያቸው ከ24 ዓመት በታችነው፡፡

### Awareness creation



Musical dramas

On top of this, a 10 days awareness creation work on Reproductive Health (RH) was carried out for 5,300 people (3,500 male, 1,800 female) through Edutainment Musical Dramas. The dramas were performed at ShoaRobit, Inewari and Deneba Towns by an Edutainment based RH club. Out of the 5,300 audiences, youth under the age of 24 account for 90%.

## ጽንስ ማስወረድ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት

ከውርጃ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያን ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከማብራራታችን በፊት በውርጃ ዙሪያ ያለውን አለማቀፋዊ እይታ ወይም አስተሳሰብ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡ ውርጃ አለማቀፋዊ ጉዳይ ሆኖ መታየት የጀመረው ከጥንት ጊዜጀምሮ ሲሆን ከ4700 አመታት በፊት ይህ ጉዳይ በዘመኑ ዋነኛ የመወያያ ጉዳይ እንደነበር በርካታ ጽሁፎች ያብራራሉ፡፡

ታሪካዊ መረጃዎች እንደሚያረጋግጡት በተለያዩ ችግሮች ምክንያት የሚከሰቱ ውርጃዎችና ሆን ተብለው የሚከናወኑ የጽንስ ማቋረጥ ተግባሮች በሶቅራጥስ፤ በፕላቶ፤ በአሪስቶትልና በሂፖቅራጥስ ዘመን ዋነኛ የሞራል፤ የሃይማኖት እንዲሁም የመንግስታት ህግጋት መወያያ ርሶች ሆነው ቆይተዋል፡፡ ከሂፖቅራጥስ በቀር የተቀሩት ሶስት ፈላስፋዎች ውርጃ የተረጋጋ ህዝብን ይዞ ለመቆየት ያስችላል ብለው ያስቡ ነበር፡፡ ውርጃን የሚቃወመው ሂፖቅራጥስ ሳይቀር አንድ ጽንስ የእናቲቱን ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ውርጃን ይደግፍ ነበር፡፡

በአለንበት ዘመን ደግሞ ውርጃ አለም አቀፋዊ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ይታያል፡፡ በመወዳደር ላይ ያሉትም ሁለት የመነጋገሪያ አጀንዳዎች አንደኛው የሽል ማደግና ሰው ሆኖ የመውለድ መብት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የእናቲቱ ሽሉን በፍላጎትዋ መሠረት የማስወረድ መብት ናቸው፡፡

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ጥንታዊ የፍልስፍና ክርክሮችና ሌሎች የዘመኑን አለማአቀፋዊ ንግግሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት አገሮች በውርጃ ዙሪያ የየራሳቸውን ህግጋት ደንግገዋል፡፡

በዚህም መሠረት አንዳንድ አገሮች ውርጃን ወንጀል አድርገው ሲደነግጉ ሌሎች አገሮች ደግሞ ውርጃን ህጋዊ አድርገው ደንግገዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ውርጃ እንደ ወንጀል በሚታዩባቸው አገሮች ውስጥ የእናቶች ህይወት አደጋ ላይ እየወደቀ ነው በማለት አንዳንድ ምሁራን ይዘግባሉ፡፡ ምክንያቱንም ሲጠቅሱ ውርጃ ህጋዊ አለመሆኑ ጽንስ የማጨናገፍ ሥራ በተሽሎኮለከና በቂ እውቀት በሌላቸው ህገ ወጦች እንዲካሄድ ምክንያት በመሆኑ ነው ይላሉ፡፡ለምሳሌ ኢፓስ የተባለ በሴቶች የስነ ተዋልዶ ጤና መብት ዙሪያ የሚሠራ ድርጅት እንደሚለው በአለም ላይ በአመት 67,000 የሚሆኑ ሴቶች ከውርጃ ጋር በተያያዘ ችግር ምክንያት እንደሚሞቱ

## Abortion and Ethiopian Penal code

Before explaining the penal code of Ethiopia with regard to abortion, we would like to say something about the global view over abortion. According to several studies, abortion has been a universal issue since antiquity which is said to exist even before 4700 years (African Journal Online, nd).

Historical facts confirm that both induced abortion and deliberate termination of pregnancy had prevailed being moral, religious and legal discourse in the time of Socrates, Plato, Aristotle and Hippocrates. Except Hippocrates, these philosophers had been purported to be supporter of abortion as they believed that abortion maintains stable population. Even Hippocrates who was against abortion had supported abortion if the life of the mother is expected to be jeopardized because of the fetus.

In the contemporary world, abortion has remained being a global controversial issue. The competing arguments are based on two major points such that the fetus right to be brought on to life and the right of the mother to abortion based on her interest or choice (African Journal Online, nd).

Considering these antiquities' philosophical arguments and other contemporary global discourses, countries have enacted different laws on abortion. Accordingly, some countries have strictly criminalized abortion in their Penal-Codes while others decriminalized it. Consequently, some scholars have reported that life of pregnant mothers in countries where abortion has been strictly criminalized is put at risk as a result of proliferation of hidden, poor professional and illegal abortion practices. For instance, as per Ipas, 67,000 women die each year from complications related with unsafe abortion-most in countries where abortion is legally restricted (Ipas, nd)).

ሲገልጽ ችግሩም ገዝፎ የሚታየው ውርጃ ህገወጥ በሆነባቸው አገሮች መሆኑን ጭምር ይጠቁማል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የአገሮች ህግጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመቀየሩና እየተሻሻለ ያለ በመሆኑ ውርጃን የማይፈቅዱ በርካታ አገሮች ህጋቸውን በማለዘብ በተወሰነ ሁኔታ ውርጃን የሚፈቅድ አንቀጽ በህጋቸው በማካተት ላይ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ኢትዮጵያም በአስራ ዘጠኝ መቶ አርባ ዘጠኝ ዓ.ም የወጣውን ህጌን በፈተሸችበት ወቅት በዘመኑ ውርጃን ለመከላከል የወጣው አጠቃላይ ህግ እንደ ተጠበቀ ሆኖ አንዳንድ መሻሻሎችን በማድረግ ውርጃ ከዚህ ቀጥሎ ባሉ ምክንያቶች በህጋዊነት መካሄድ እንደሚችል ፈቅዳለች፡-

Dynamically, laws of countries pertaining to abortion have been changing and improved from time to time. As a result, now, most of the countries liberalized their laws. Similarly, Ethiopia has also liberalized and revised its penal code of 1957 sections (528 -535) which was permitting abortion very limitedly. According to the revised Criminal Code of the Federal Republic of Ethiopia, not withstanding to the legal prohibition of abortion in the 1957 penal-code, abortion allowed by law in the following conditions:


Young women BDS & vocational skill training


Musical show

- እርግዝናው የተከሰተው በአስገድዶ መደፈር ምክንያት ወይም የስጋ ዝምድና ባላቸው ጥንዶች ከሆነ
- የእርግዝናው መቀጠል የእናትየውን ወይም የጽንሱን ጤና ወይም ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል ሆኖ ከተገኘ
- ጽንሱ ጤናማ ሆኖ የማይወለድ መሆኑ ሲገመት
- ጽንሱ በእናቲቱ አካላዊም ሆነ አምሮአዊ ጤንነት ላይ ጉድለት ወይም ጉዳት ያደርሳል ተብሎ ሲገመት
- እናቲቱ ልጅ ለማሳደግም ሆነ ሀላፊነትን ለመሸከም የማትችል ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ከሆነ
- የእናቲቱ ህይወት ፍጹም አደጋ ላይ ሆኖ ጽንሱን ከማስወረድ በቀር ህይወቷን ማትረፍ የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ

- when the pregnancy results from rape or incest;
- when continuance of the pregnancy endan gers the health or life of the woman or the fetus;
- in cases of fetal abnormalities;
- for women with physical or mental disabili ties;
- for minors who are physically or psycho logically unprepared to raise children;
- in the case of grave and imminent danger that can be averted only through immediate pregnancy termination